ተግባር (Tegbar)
Ethiopian Democratic Action League
tegbar.ethiopia@gmail.com * www.tegbar.org

# የኢትዮጵያ ሁለት ሺህ ዓመት የአምባገነን አገዛዝ የሚያከትምበት!

ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ተግባር ሊግ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ የቀረበ ጥሪ

የፊታችን መስከረም ወር ኢትዮጵያ ወደ አዲስ ዘመን የምትሸጋገርበት ነው። ይህን ወቅት በፈንጠዝያ ለመቀበል የመለስ ዜናዊ አገዛዝና ተባባሪዎቹ ዝግጅት ከጀመሩ ሰንብተዋል። እንደሚታወቀው፣ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ ህጋዊ መሪዎች በእስር እየማቀቁ ይገኛሉ፣ ህዝብ ድምጹን ተቀምቷል፣ ዜጎች ላይ የሚፈጸመው ግፍ፣ ድብደባና ግድያ በሰፊው ቀጥሏል። ከወያኔ/ኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎቹ በስተቀር አብዛኛው ህዝብ በኑሮ ውድነት፣ ሥራ አጥነት፣ በበሽታ፣በረሃብ፣ በአጠቃላይ እጅግ በከፋ የድህነት አለንጋ እየተገረፈ ይገኛል። ይህ እስከመቼ ነው የሚቀጥለው? መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ እስከመቼ ድረስ ነው የኢትዮጵያን ህዝብ ረግጠው፣ አዋርደው፣ ስብዕናውን ገፈው፣ መሪዎቹን አፍነው የሚገዙት?

አዲሱ ዘመን ለኢትዮጵያ አዲስ ምዕራፍ የምንከፍትበት፣ የአምባገነን አገዛዝ እንዲያከትም የምናደርግበት ወቅት ይሁን የሚለውን መርህ ተግባር ሊግ ይደግፋል። ቅንጅት ለኢትዮጵያ ህዝብ መሪዎቹን እንዲያድን ያቀረበውን ህዝባዊ ጥሪ፣ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የተላለፈውን መልዕክት በመደገፍ ተግባር ሊግ በበኩሉ የሚከተለውን ጥሪ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ያቀርባል፤

1ኛ/ ከፊታችን ነሀሴ 1 ቀን 1999 እስከ መስከረም 1 ቀን 2000 ዓ/ም የኢትዮጵያ ህዝብ በአንድነት ተነስቶ የግፍ አግዛዝ በቃኝ የሚልበት ወቅት እንዲሆን።

2ኛ/ ይህ የትግል ወቅት ውጤታማ እንዲሆን ዝግጅቱ ከአሁኑ እንዲጀምር።

3ኛ/ ዝግጅቱም የሚከተሉትን ዕቅዶች እንዲያካትት ለመጠቆም እንወዳለን፤

ሀ/ ከአሁን ጀምሮ እስከ መስከረም 1 ቀን ድረስ የተቀናጀ፣ ሁሉም ነፃ የራዲዮ ዝግጅቶች፣ ድህረ ገጾችና ሌሎችም መገናኛ ብዙኃን የሚተባበሩበት የቅስቀሳ ፕሮግራሞች ማሰራጨት ።

ለ/ ከፊታችን ነሀሴ 1 እስከ መስከረም 1 ሁለገብ ሀገር–አቀፍ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ማካሄድ፣ በተለይም ዋና ዋና መንገዶችን፣ ወያኔ የሚቆጣጠራቸውን ንግዶችንና የመንግስት መሥሪያ ቤቶችን አቅምና ሁኔታዎች በፈቀዱባቸው ቦታዎችን ሁሉ መዝጋት። በውጭ ሀገር ያሉ የኢትዮጵያ ኢምባሲዎችን በነሀሴ ወር ውስጥ በተለያዩ ቀናት መዝጋት።

ይህ ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ ወያኔ/ኢህአዴግ ላይ ተቃውሞውን የሚገልጽበትና ዕብሪተኛው ወያኔ ለህዝብ ድምጽ ተገዢ እንዲሆን የሚደረግበት ጊዜ ይሆናል።

የዚህ እንቅስቃሴ ወይም ዘመቻ መሳካት የሚለካው በሚከተሉት ነው፤

ሀ/ የፖለቲካ እስረኞች፣ ማለትም የቅንጅት አባላትና መሪዎች፣ የኦነግ አባላት፣ የአርበኞች ግንባር አባላት፣ የህወሓት አባላት (ሰዬ አብረሃምና አብረዋቸው በግፍ የታሰሩት)፣ ጋዜጠኞች፣ የሙያ ማህበራት አባላት እና ሁሉም ወያኔ/ኢህአዴግን በመቃወም የታሰሩት ሲፈቱ።

ለ/ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በጠሩት የስላም ጉባኤ ወያኔ/ኢህአዴግ ሲሳተፍ፣ አሻፈረኝ ካለም በህገወጥነትና በጉልበት የያዘውን ስልጣን እንዲለቅ ሲደረግ።

ነፃነት፣ ፍትህ፣ ዴሞክራሲ ለኢትዮጵያ ህዝብ!

የተግባር ሊግ ኢትዮጵያ ጠቅላይ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ
አዲስ አበባ
ሰኔ 7 ቀን 1999